# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

## ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
## <u>የቀረበ አስቸኳይ የትግል ጥሪ</u>

**ይድረስ ለኢትዮጵያ ሕዝብ**

በአቶ መለስ ዜናዊ የሚመራው የኢሕአዴግ/ሕወሓት መንግሥት ከጥቅምት ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም ጀምሮ በተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች፥ የሲቪክና የሙያ ማኅበራት፥ የነፃው ፕረስ ሃላፊዎችና መሪዎች፥ አባላትና ደጋፊዎች እንዲሁም በአዲስ አበባ ሰላማዊ ሕዝብ ላይ ጦርነት አውጆ ከፍተኛ የእልቂት ዘመቻውን ተያይዞታል።

ሕጋዊና ሰላማዊ ተቃውሞን ከጦርነት እወጃ ለይቶ ማየት የተሳነውና ከአሥራ አራት ዓመታት በሥልጣን ላይ መቆየት በኋላም እንኳ ከጠመንጃ የአመፅ ፖለቲካ ሊላቀቅ ፈጽሞ ያልቻለው የኢሕአዴግ አገዛዝ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሠረታዊና ሕገ-መንግሥታዊ መብቱን ለማስከበር ያቀረበውን ሰላማዊና ቀላል ጥያቄ ማስተናገድና በሚገባ መረዳት አቅቶት የባዕድ ኃይል ብቻ ሊሰራው ይችላል ተብሎ በሚገመት ደረጃ አረመኔአዊ ጭካኔ የተመላበት ጭፍጨፋ በንፁህ ዜጎች ላይ እያደረሰ ይገኛል።

ይኸ ገዥ ቡድን መንግሥት ከሚያሰኙ ባህርያት እየተላቀቀ ተራ የውንብድናና የአረመኔ ተግባር ላይ በመሰማራቱ በአገራችን ላይ መንግሥት አለ ማለት የማይቻልበት ሁኔታ እየተፈጠረ ነው። ውድ አገራችን ኢትዮጵያን መንግሥት አልባ ወደምትሆንበት አደገኛ ሁኔታ እየወሰዳት ይገኛል። ከዚህ ፀረ-ሕዝብና ፀረ-አገር ኃይል ትዕዛዝ ተቀብሎ በሰላማዊ ኢትዮጵያውያን ላይ በሚሰነዘረው ሕገ-ወጥ እርምጃ ተካፋይና ተሳታፊ የሚሆን በተለይም በአዛዥነት ላይ ያሉ ሁሉ ከዛሬ ጀምሮ የዚህ ወንጀል ተባባሪ እንደሆኑ መቆጠር ይኖርባቸዋል።

ስለሆነም ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይኸንን ከመንግሥት ሃላፊነት ወርዶ እራሱን በውንብድንናና በአመፅ ተግባር ላይ እያሰማራ ያለ ቡድንን እኩይ ፀረ-ሕዝብ የወንጀል ተግባር በተናጠል ሳይሆን በአንድነት ሊቋቋመው ያስፈልጋል።

**ጀግናው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!**

ትዕግሥትህን ከፍርሃት፥ አርቆ አስተዋይነትህን ከድንቁርናና ከአለማወቅ የቆጠረው ይኸ ጋጠ-ወጥ ቡድን ከአሁን በኋላ የወፊት ዕድልህ ወሳኝ ሊሆን አይችልም። ይኸ የኢትዮጵያንም ሆነ የሕዝቧን ጥቅም ለማስጠበቅ ምንም ዓይነት ብቃቱም ሆነ ፍላጎቱ እንደሌለው በተግባርና በአደባባይ እያስመሰከረ ያለ ሃላፊነት የጎደለው ደንታ-ቢስ ቡድን ዓለም በመሰከረልህ ጨዋነትና ቆራጥነት አሁንም በተለመደው አኩሪ ባህሪህ በፖለቲካ ድርጅት፥ በጎሣ፥ በቋንቋ፥ በሐይማኖት፥ በአካባቢ፥ በሙያ፥ ወዘተ... ሳትከፋፈል በያለህበት በአስቸኳይ በአካባቢ በአካባቢህ እየተደራጀህና ሃላፊዎችህን እየመረጥክና እየሰየምክ ድምፅህን ለማስከበር የጀመርከውን ሰላማዊና ሕጋዊ ትግል እንድትቀጥልና በሰላማዊ መንገድ የየአካባቢ ፀጥታህን እንድታስጠብቅ ይሁን። ይኸም ሲሆን አሁንም

ገዥው አካል እንደሚመኘውና እንደሚያውጠነጥነው ማንንም ኢትዮጵያዊ በማንኛውም ድርጅት አባልነቱም ሆነ በቋንቋው ወይም በአካባቢ፥ ወዘተ.... ምክንያት ያገለለ ወይም በጠላትነት እንዲታይ ባደረገ መልኩ ፈጽሞ እንዳይሆን ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል፡፡

ይኸ ትግል የአንድን ብሔረሰብ ወይም ክልል ወይም ድርጅት ጥቅም ለማስከበር የሚደረግ ሳይሆን፥ በነፃ ፍላጎቱ ይሆኑኛል ብሎ ያመነባቸውን ተወካዮቹን እንዳይመርጥ መብቱ የተነፈገውን የትግራይ ሕዝብ ይሁን፥ በብዙ መስዋዕትነት ምርጫ አካሂዶ ድምፁን የተነጠቀው በሁሉም አካባቢ ያለውን ዜጋ ሁሉ፥ በአጭሩ በሁሉም የአገሪቱ ክፍል የሚገኘውን የጠቅላላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ መብት ለማስከበርና የሥልጣኑ ምንጭና ባለቤት መሆኑን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሚያረጋግጥበት ሰላማዊና ፍትኃዊ ትግል ነው፡፡

ይኸ እንቅስቃሴ ከአሁን በፊት በተደጋጋሚ እንዳሳሰብነው ሁሉ በተናጠልና በየተራ እየተነሳ በተናጠልና በየተራ በሚመታበት መልክ መደረግ አይኖርበትም፡፡ ትግሉ በጠቅላላ አገር-አቀፍና የሁሉም መሆን ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም ይኸ ሕጋዊና ሰላማዊ የመብት ማስከበር ትግል በአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን በመላ አገሪቱ ከዛሬ ጀምሮ መቀጣጠልና መካሄድ አለበት፡፡

በመሆኑም ከአሁን በፊት ለመስከረም ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም በአገሪቱ ዋና ዋና ከተሞችና በዓለም-አቀፍ ደረጃ "የሰላም፥ የዜጎች አንድነት ትስስርና የዴሞክራሲ የድጋፍ ሰልፍ" በሚል ከቅንጅቱ ጋር በጋራ ተጠርቶ የነበረው የድጋፍ ሰልፍ እንዲደረግ በታሰበባቸው ቦታዎች ሁሉ ከሌሎች አገር-ወዳድና ዴሞክራት ታጋይ ወገኖች ጋር በመምከር በቅርብ ቀን በተከታታይ በምናቀርባቸው መግለጫዎች በሚወሰን ቀን ሕዝቡ አቅራቢያ ወደሆኑት ከተሞች በከፍተኛ ቁጥር በመገኘት "ለሰላም፥ ለአንድነትና የታሰሩ ዜጎችን ለማስፈታት" በሚል ዓላማ ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ እንዲዘጋጅ ጥሪያችንን በአክብሮት እናቀርባለን፡፡ በውጭው ዓለም ያለው ኢትዮጵያዊ ደግሞ ማክሰኞ ጥቅምት ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም (November 8, 2005) በዚሁ ዓላማና መንፈስ መሠረት በታላላቅ ከተሞች ላይ ሰላማዊ ሰልፍ እንዲወጣና ሕዝባችን በከፍተኛ ቁጥር ተገኝቶ ተሳታፊ በመሆን ለወገኑ ያለውን አጋርነት፥ በወገናችን ላይ አገዛዙ እየደረሰ በአለው አሰቃቂ ሁኔታ የተሰማውን ቁጭት፥ ኢትዮጵያዊ አንድነቱንና ቁርጠኝነቱን እንዲያሳይ በአክብሮት እንጠይቃለን፡፡

ሸብር ይቁም!!
የታሰሩ ይፈቱ!!
የኢትዮጵያ ሕዝብ የተነጠቀ መብቱን በጋራ ትግሉ ያስመልሳል!!!!

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)

ጥቅምት ፳፫ ቀን ፲፱፻፱፰ ዓ/ም